ከታህሣሥ 28-ጥር 10 ቀን

1. **ወአመ ሰሙን**

ወአመ ሰሙን እለት ወሰድዎ ከመይግዝርዎ/2/

ወሰመይዎ ስሞ ኢየሱስ/2/

በስምንተኛው ቀን ወሰዱት ይገዝሩት ዘንድ/2/

ስሙንም አሉት ኢየሱስ/2/

2. **ቀድሞ የነበረው**

ቀድሞ የነበረው አምላክ

በታላቅ ዙፋን ላይ አምላክ

በስጋ ተወልዶ አምላክ

መጣ ሊዛመደን አምላክ

አምላክ አምላክ መድኃኔዓለም/2/

ለሰው ልጆች አዳኝ አምላክ

ከኃጢያት ቁራኛ አምላክ

በበረት ተወልዶ አምላክ

በበረት ላይ ተኛ አምላክ

አዝ---

በበረት ተኝቶ አምላክ

ተጠቅልሎ በጨርቅ አምላክ

ሊያዩት ገሠገሡ አምላክ

ነገስታት ከምሥራቅ አምላክ

አዝ---

ለጥ ብለው ሲሰግዱ አምላክ

የምስራቅ ነገስታት አምላክ

ከበው ያዩ ነበር አምላክ

እንስሳት በበረት አምላክ

አዝ---

ነገስታት ሊሰግዱ አምላክ

እንስሳት ካዩማ አምላክ

የአዳም ልጅ ያመስግን አምላክ

በጥዑመ ዜማ አምላክ

### 3. አንቺ ቤተልሄም/በመቀባበል/

አንቺ አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ መሬት

ባንቺ ተወለደ የዓለም መድኃኒት

ለአዳም ክብር ሲሻ ቤተልሔም

ለሁሉም ሰላም ቤተልሔም

ዛሬ ተወለደ ቤተልሔም

ከድንግል ማርያም ቤተልሔም

አዝ---

እጅ መንሻ አቀረቡ ቤተልሔም

የምስራቅ ነገሥታት ቤተልሔም

በከብቶች በረት ቤተልሔም

ተኝቶ ላገኙት ቤተልሔም

አዝ---

እስራኤል ህዝቤን ቤተልሔም

የሚጠብቃቸው ቤተልሔም

ካንቺ ይወጣል ብሎ ቤተልሔም

እንደነገራቸው ቤተልሔም

### 4. የዓለም መድኀኒት

የዓለም መድሐኒት የተወለደብሽ

አንቺ ቤተልሔም የተቀደሽ ነሽ

የአማልክት አምላክ ንጉሰ ነገስት

ኀያላን በሙሉ የሚሰግዱለት

በጨርቅ ተጠቅልሎ ተኛ በበረት

አዝ

አዋቂዎች ሁሉ በቅን አሳባቸው

ወደ አንቺ ተጓዙ ኮከብ ቢመራቸው

አዝ

ለተከታይ ትውልድ ምሳሌ ለመሆን

ሰግደው ገበሩለት ወርቅ ዕጣን ከርቤን

አዝ

የሚያድለው ጌታ ዕውቀት ለሕጻናት

የሚመሰገነው በአፈ መላዕክት

ከእንስሳት ጋራ አደረ በበረት

አዝ

በስጋ ተወልዶ በረቂቅ ምስጢሩ

ሰውና መላእክት በአንድ ላይ ዘመሩ

## 5. የጥበብ ሰዎች መጡ

<u>የጥበብ ሰዎች መጡ</u>(2) ሰምተውት በዜና

ያበራላቸው ኮከብ እንደፋና/2/

ሰማይና ምድር የማይወስኑት/2/

ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት/2/

ዘጠና ዘጠኙ መላዕክቱን ትቶ/2/

አገኘነው ዛሬ በበረት ተኝቶ/2/

አዝ---

ድንግል እመቤቴ ሰላም ይድረስሽ/2/

ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ/2/

ከአንቺ ተወለደ የዓለም መድኅን/2/

ኩነኔን አጥፍቶ ክብርን ሊያወርሰን/2/

አዝ---

ጌታችን ሲወለድ በቤተልሄም/2/

ኀዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም/2/

እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት/2/

ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት/2/

አዝ---

ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ/2/

የእስራኤል ንጉሥወዴት ነው እያሉ/2/

እጅ መንሻውን ሰጡት እንደየሥርዓቱ/2/

ዕጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግሥቱ/2/

አዝ----

## 6. ሣር ቅጠሉ ሰርዶው

ሣር ቅጠሉ ሰርዶው ሰንበሌጥ ቄጤማው

በዚያች ወር በዚያች ቀን ለምለም የነበረው

በእልልታ ዘመሩ በደስታ ተሞልተው

ጌታ መወለዱን የምስራች ሰምተው

እልል በይ ቤተልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ

የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ/2/

ያ ትጉህ እረኛ ሳለ በትጋት

ብርሃንን ለበሰ በእኩለ ለሊት

ጥሪ ተደርጎለት ከሰማይ ሰራዊት

ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት

አዝ------

የእረኝነት ስራ ተንቆ እንዲቀር

ብሎ ሰው በልማድ ደንግጎ ነበር

አምላክ የመረጠው መሆኑን እረኛ

ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ

አዝ------

የተነበዩለት ነቢያት በሙሉ

ጌታ ተወለደ የምስራች በሉ

ሰውን በመውደዱ ሰማያዊው ንጉስ

ይኸው ተወለደ እኛን ሊመቀደስ

አዝ----

የሩቅ ምስራቅ ሰዎች ሰብአ ሰገል ሰምተው

ሊሰግዱለት መጡ በኮከብ ተመርተው

ዕጣንና ከርቤ ወርቁም አመጡ እንደየሥርዓቱ መነሻ ሰጡ

አዝ-----

ስለተወለደ መድኅን የእኛ ተስፋ /2/

በደል ተወገደ ኀጢያትም ጠፋ/2/

### 7. እሰይ እሰይ ተወለደ

እሰይ አሰይ ተወለደ /2/

ከሰማየ ሰማያት ወረደ

ከድንግል ማርያም ተወለደ

እሱ ባይወለድ እሰይ እሰይ ቸሩ አባታችን እሰይ አሰይ

መች ትገኝ ነበር እሰይ እሰይ ገነት ምድራችን እሰይ እሰይ

አዝ------

ብርሃን ወጣላቸው እሰይ እሰይ ለመላ ህዝቦቹ እሰይ እሰይ

በጨለማ ጉዞ እሰይ እሰይ እንዲያ ሲሰላቹ እሰይ እሰይ

አዝ-----

እንደ ጠል ወረደ እሰይ እሰይ ከሰማይ ወደእኛ እሰይ እሰይ

ወገኖቹን ሊያድን እሰይ እሰይ ከኃጢያት ቁራኛ እሰይ እሰይ

እዝ------

እግዚአብሔር አብ ላከ እሰይ እሰይ አንድያ ልጁን እሰይ እሰይ

እርሱ ወዷልና እሰይ እሰይ እንዲሁ ዓለሙን እሰይ እሰይ

### 8. በልዩ ልደቱ

በልዩ ልደቱ እሰይ እሰይ በተገኘው ጸጋ እሰይ እሰይ

ስለተዋሐዱ እሰይ እሰይ መለኮት ከስጋ እሰይ እሰይ

እሰይ እሰይ ተወለደ/2/

ከሰማየ ሰማያት ወረደ/2/

ከቅድስት ድንግል ተወለደ

እናንተ ሕፃናት እሰይ እሰይ በጣም ተደሰቱ እሰይ እሰይ

ብርሃን ከተገኘ እሰይ እሰይ ዛሬ በልደቱ እሰይ እሰይ

አዝ-------

ትንቢቱ ሲፈጸም እሰይ እሰይ ዛሬ በልደቱ እሰይ እሰይ

ዕጣንና ከርቤ እሰይ እሰይ ወርቅንም አየን እሰይ እሰይ

## 9. በበረት የተኛው

በበረት የተኛው ቅዱሱ ሕፃን

ለዓለሙ ሁሉ ሆነለት መድኅን

ምስክር ሊሆኑ ለፍጹም መንግሥቱ

ትንፋሽ ገበሩለት ከበው እንስሳቱ

እሰይ የምስራች ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ

ጌታ ተወለደ ከድንግል ማርያም

## 10.በቤተልሄም ተወለደ

በቤተልሄም ተወለደ (2)አማኑኤል/2/

እምዘርዐ ዳዊት (4) ተወልደ አማኑኤል

ትርጉም፡-ከዳዊት ዘር አማኑኤል በቤተልሄም ተወለደ

## 11.በጎል ሰከበ

በጎል ሰከበ በአፅርቅት ተጠብለለ/2/

ቤዛ ኩሉ ዓለም(2)ዮም ተወልደ/2/

ትርጉም ፡-

በበረት ተኛ በጨርቅም ተጠቀለለ/2/

የዓለም መድኅኒት (2)ዛሬ ተወለደ

## 12.ኢየሩሳሌም በሆንን

እንደ ዮሴፍ ወይ እንደ ሰሎሜ በሆንን/2/

ኢየሩሳሌም/3/በመሆንን አምላክ ሲወለድ ባየን

እንደ እረኞች እንደ ሰብአ ሰገል በሆንን/2/

ኢየሩሳሌም/3/ በሆንን አምላክ ሲወለድ ባየን

## 13. የምስራች ደስ ይበለን

የምስራች ደስ ይበለን/2/

የዓለም መድሃኒት ተወለደልን/2/

የምስራች ደስ ይበለን/2/

ንጉስ ሄሮድስ ይህን ሲሰማ/2/

ፈልጋችሁ አምጡት በቀን በጨለማ/2/

ሰብአ ሰገል እንደታዘዙት/2/

በኮከብ ተመርተው ሕፃኑን አገኙት/2/

ሰገዱለት ከመሬት ወድቀው /2/

ወርቅና ዕጣን ከርቤውን በረከቱን ሰጥተው/2/

የምስራች ደስ ይበለን/2/

ጌታችን ተወልዶ አይተነው መጣን2/

የምስራች ደስ ይበለን

### 14.ዮም ፍሥሓ ኮነ

ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ/2/

እም ቅድስት ድንግል/2/ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ/2/

ትርጉም፡-ዛሬ ኢየሱስ ክርስቶስ በመወለዱ ደስታ ሆነ ከቅድስት ድንግል

### 15.አንፈራጹ

አንፈራጹ ሰብአ ሰገል/2/

አምኃ ሆሙ አምፁ መድምመ/2/

ትርጉም፡-

### 16.አማን በአማን

አማን በአማን/2/ መንክር

አማን በአማን በአማን መንክር ስብሐተ ልደቱ/2/

ትርጉም፡-እውነት የልደቱ ምሥጋና ድንቅ ነው

### 17.ተወልደ ኢየሱስ

ተወልደ ኢየሱስ በቤተልሔም(2)ዘይሁዳ በቤተልሄም /2/

አዋልደ ጢሮስ አሜሃ ይሰግዳ/2/ በቤተልሄም/2/

ትርጉም፡-ኢየሱስ የይሁዳ ዕጣ በምትሆን በቤተልሄም ተወለደ

የጢሮስ ሴቶች ልጆችም ያንጊዜ ይስግዳሉ

### 18.ቤዛ ኩሉ ዓለም

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ /2/

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ /2/

የዓለም ሁሉ መድኀኒት ዛሬ ተወለደ/2/

የዓለም ሁሉ መድኀኒት ዛሬ ተወለደ/2/

### 19.ለዘተወልደ

ለዘተወልደ እም ቅድስት ድንግል ምንተ ንብሎ

ናስተማስሎ ለመድኀኒነ/2/

አርዌ ገዳምኑ አንበሳ ወሚመ(2)ከራድዮን/2/

ትርጉም፡-ከእመቤታችን የተወለደው ምን ብለን እንጠራዋለን።

መድኀኒታችን  ኢየሱስ ክርስቶስን በምን እንመስለዋለን በዱር አውሬ

ነው? በእንስሳ ወይስ ከራድዮን በሚባል ወፍ ነው።

### 20.ወወለደት

ወወለደት ወልዳ ዘበኩራ/2/

መንጦላዕተ ደመና ሠወራ/2/

ትርጉም፡-የበኩር ልጇን ወለደች የደመና መጋረጃም ጋረዳት

/ሰወራት/

### 21.በኮከብ መጹዑ

በኮከብ መጽዑ /2/ ሰብአ ሰገል /2/

ለአማኑኤል /4/ ይስግዱ ሰብአ ሰገል /2/

በኮከብ መጡ መጡ ሰብዐ ሰገል/2/

ለአማኑኤል /4/ ሊሰግዱ ሰብአ ሰገል

### 22. እምርኁቅ መጽኡ

እምርሁቅ መጽኡ/2/ ሰብአ ሰገል/2/

ለአማኑኤል/4/ይስግዱ ሰብአሰገል

ትርጉም፡-ለአማኑኤል ይሰግዱለት ዘንድ የጥበብ ሰዎች ከሩቅ ሀገር

መጡ

### 23.እስመ እም ዘርአዳዊት

እስመ እም ዘርአዳዊት ዘመጽአ/2/

በቤተልሔም ዘይሁዳ/2/

ትርጉም፡-ለይሁዳ ዕጣ ከምትሆን ከዳዊት ዘር መጥቷልና

### 24.ስብሐት ለእግዚብሔር

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት/2/

ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ/3/

አሜን ሃሌ ሉያ

ትርጉም፡-ለእግዚአብሔር በሰማያት ምስጋና ይገባዋል በምድር እርቅ ተጀመረ ለሰው ግዕዛኑ /ነፃነቱን/ሊሰጠው

### 25.እንዲሆነን ቤዛ

እምሰማያት ወረደ ወእም ማርያም ተወልደ ተወልደ/2/

ከመ ይኩን ቤዛ/2/ ለኩሉ ዓለም ለብሰ ሥጋ ማርያም /2/

ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ/2/

እንዲሆነን ቤዛ/2/ ለዓለም ሁሉ ለበሰ የማርያምን ሥጋ/2/

### 26.መጽአ ከመይቤዙ

መጽአ ከመይቤዙ ዓለም/2/

የሀበነ ሰላመ;ጋዳ ያበውኡ ቁርባነ /2//

ትርጉም፡-ዓለምን ለማዳን መጣ ሰላምን

ይስጠን ዘንድ እጅ መንሻም ያአቀርባሉ

### 27. ይኸው ተወለደ

ይኸው ተወለደ <u>የዓለም መድኃኒት/3/</u>

እሰይ ተወለደ የዓለም መድኃኒት/3/

ትንቢት ተናገሩ <u>ነቢያት በሙሉ/3/</u>

አምላክ ቀዳማዊ <u>ይወርዳል እያሉ/3/</u>

ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ <u>በሙሉ</u>/3/

የእስራኤል ንጉሥ <u>ተወልዷል እያሉ/3/</u>

ሰብአ ሰገል መጡ <u>ይዘውእጅ መንሻ /3/</u>

ወርቅ ዕጣኑ ከርቤ <u>ለማርያም እጅ መንሻ/3/</u>

በሶርያ ታየ ፈጣሪ እንግዳ /3/

ብሥራተ ልደቱን ለሁሉ ሊያስረዳ/3/

ሕፃናት እንሂድ ከልደቱ ቤት/3/

ውኃው ሆኗልና ማርና ወተት/3/

**28.ፍሥሐ ለኲሉ**

ነዋ ተወልደ መድኅኔዓለም/2/

ፍሥሐ ለኲሉ ዘየአምን/4/

ዛሬ ተወለደ የዓለም መድኃኒት/2/

ደስታ ነውና ለሚያምኑት/4/

**29.መጽአ ወልደ አምላክ**

መጽአ ወልደ አምላክ/2/ወልደ አምላክ /2/

ለቢሶ ሥጋ ማርያም ሥጋ ማርያም ወጸዊዖ ነፍሳተ ኀይል

ትርጉም፡-የአምላክ ልጅ መጣ የማርያምን ሥጋ ለብሶ የኀይልን ነፍሳት ጠራቸው

30. **በጎለ እንበሳ**

በጎለ እንስሳ /4/

በጎለ እንስሳ ተወለደ አማኑኤል/4/

በእንስሳት በረት /4/

ተወለደ አማኑኤል /4/

**31. ሶበ ሰማዕነ**

ሶበ ሰማእነ ዜናከ መጻእነ ኀቤከ/2/

መጻእነ/4/

አንቺ ቤተልሔም የዳዊት ከተማ

የምስራች ቃሉ በአንቺ ቤት ተሰማ

ወንድ ልጅ ተሰጠን ሕፃን ተወለደ

አስጨናቂው ዘመን በእርሱ ተወገደ

ሰውና መላእክት በአንድ ላይ ዘመሩ

የእግዚአብሔርን ክብር ለዓለም መሰከሩ

ምስጋና በሰማይ ለእግዚአብሔር ይሁን

ሰላም ለሰው ልጆች በምድር ላይ ይስፈን

እናትና ልጇ ታዩ ፀሐይ ለብሰው

የእግዚአብሔር መላእክት ከፊታቸው

ወድቀው

በከብቶች በረት አምላክ ተወለደ

የነገሥታት ንጉሥ ሞትን አስወገደ

ድንቅ መካር ኃያል የሰላም አለቃ

ጌታ ሆይ በስምህ ግዞቱ አበቃ

ሰላምን የሚሰጥ አልፋና ዖሜጋ

የእስራኤል ንጉሥ ተገልጾአል በሥጋ

**32. አስተርአየ ገሐደ**

አስተርአየ ገሐደ/4/

በለቢሰ ሥጋ ኮነነ ዘመደ /4/

ትርጒም:- በግልጥ ታየ ሥጋችንን በመልበስ ዘመድ ሆነን

## የወርኀ ጥር መዝሙራት

### የቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ መዝሙር ጥር 4 ቀን

**33.ዮሐንስ ዘረፈቀ**

ዮሐንስ ዘረፈቀ ውስተ ሕጽኑ/2/

ዮሐንስ ዘረፈቀ ውስተ ሕጽኑ/4/

ትርጉም፡-ከጌታ ዘንድ የተጠጋው ዮሐንስ

**34.ሰባኬ ወንጌል**

ሰባኬ ወንጌል ሐዋርያ ትንቢት ለቤተክርስቲያን

ዘይደምፅ ቀርን ነባቢ ለቤተክርስቲያን/2/

ዮሐንስ ኮከብ ዘኤፌሶን ዐምደ ብርሃን ዘፍጥሞ መልአክ

ዘበምድር ዘበምድር መልአክ/2/

ትርጉም፡-የትንቢት ሓዋርያ ለቤተክርስቲያን በመለከት ድምፅ የሚናገር ዮሐንስ የኤፌሶን ኮከብ የፍጥሞ የብርሃን ዐምድ ምድራዊ መልአክ ነው

**35.ቀዳሚሁ ቃል**

ቀዳሚሁ ቃል ውእቱ ቃል/2/

ቃል ሥጋ ኮነ ይቤ ዮሐንስ/4/

ትርጉም፡-በመጀመሪያ ቃል ነበረ ያ ቃል ሥጋ ሆነ አለ ዮሐንስ

የቅድስት ሥላሴ መዝሙር

ጥር 7 ቀን

**36.ነአምን በአብ**

ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ በወልድ/2/

ወነአምን(4)ነአምን በመንፈስ ቅዱስ/2/

እናምናለን በአብ እናምናለን በወልድ በወልድ/2/

እናምናለን/4/ እናምናለን በመንፈስ ቅዱስ/2/

**37.ስብሐት ለአብ**

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ/2/

ለዘአብጽሐነ እስከ ዛቲ ሰዓት/2/

ትርጉም፡-እስከዚህች ሰዓት ላደረሰን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል

**38.አማን አማን**

አማን በአማን አማን በአማን መንግስተ ሥላሴ/2/

መንግስተ ሥላሴ ዘለዓለም/2/

ትርጉም፡-እውነት በእውነት የሥላሴ መንግስት ዘላለማዊ ነው

**39.ሥላሴ ትትረመም**

ሥላሴ ትትረመም ወትትነከር/2/

ሥላሴ ትትረመም ወትትነከር/4/

ትርጉም፡-ሥላሴ ይደነቃል

የዘመነ ጥምቀት መዝሙር

ጥር 10 እና 11 ቀን

### 40.በፍሥሀ ወበሰላም

በፍሥሐ /2/ ወበሰላም/2/

ወረደ ወልድ/4/ ወልድ ውስተ ምጥማቃት/2/

ትርጉም፡-በደስታ ወልድ ወደ መጠመቂያ ሥፍራ ወረደ

### 41.ወረደ ወልድ

ወረደ ወልድ /6/

እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት/4/

ትርጉም፡-ወልድ ክርስቶስ ከሰማያት ወደ ወንዞች ወረደ

### 42.ሖረ ኢየሱስ

ሖረ ኢየሱስ/6/

እም ገሊላ ኀበ ዮሐንስ/4/

ትርጉም፡-ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ዩሐንስ ሔደ

### 43.ኢየሱስ ሖረ

ኢየሱስ ሖረ ሀገረ እሴይ/2/

ዮሐንስ አጥመቆ በማይ/4/

ትርጉም፡-ኢየሱስ ወደ እሴይ ሀገር ሔደ ዮሐንስም በውሃ አጠመቀው

### 44.እግዚኡ መርሐ

እግዚኡ መርሐ ዮርዳኖስ አብጽሐ/2/

ወበህየ ዮሐንስ ወበህየ ፍጹመ ተፈሥሐ/2/

ጌታውን መራና ዮርዳኖስ አደረሰው/2/

በዚህም ዮሐንስ በዚህም በፍጹም ደስ አለው/2/

### 45.ከድንግል ተወልዶ

ከድንግለ ተወልዶ እኛን ሊቀድስ

ተጠመቀ ኢየሱስ ባሕረ ዮርዳኖስ

መጥምቁ ዩሐንስ ምንኛ ታደለ

ከነቢያት ሁሉ ሥልጣኑ ከፍ አለ

አዝ-----

ትንቢቱ ሊፈጸም እስቦ ክርስቶስ

ተጠምቆ አዳነ በባህረ ዮርዳኖስ

አዝ-----

ምሥጢረ ሥላሴ ታየ የዚያን ለታ

ምን ይከፈለዋል ለአምላክ ውለታ

አዝ----

እመቤቴ ማርያም ምንኛ ታደልሽ

ከአዳም ልጆች ሁሉ አንቺ ተመረጥሽ

እዝ----

ቸሩ አምላካችን መድኀኔዓለምን

ኑ እናመስግነው በአንድነት ሆነን

**46.ኀዲጎ ተስዓ**

ኀዲጎ ተስዓ ወተሰዓተ ነገደ ነገደ/2/

ማዕከለ ባሕር/4/ቆመ ማዕከለ ባሕር/2/

ትርጉም፡-ዘጠና ዘጠኙን የመላእክት ነገድ ትቶ በባሕር መካከል ቆመ

**47.ኀዲጎ ተስዓ**

ኀዲጎ ተስዓ ወተሰዓተ ነገደ/2/

ማእከለ ባህር ቆመ ማዕከለ ባህር/2/

ትርጉም፡-ዘጠና ዘጠኙን የመላእክት ነገድ ትቶ በባህር መካከል ቆመ

**48.ዮሐንስ አጥመቆ**

ዮሐንስ አጥመቆ ለኢየሱስ/2/

በፈለገ ዮርዳኖስ በፈለገ ዮርዳኖስ/2/

ትርጉም፡-ዮሐንስ ኢየሱስን በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቀው

**49.መጽአ ቃል**

መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል/2/

ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር/2/

መጣ ቃል ከደመና እንዲህ የሚል/2/

የምወደው የማፈቅረው ልጄ ይህ ነው/2/

### 50.ተጠምቀ ሰማያዊ

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ /2/

ተጠምቀ ሰማያዊ በዕደ መሬታዊ/2/

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ /2/

አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በልደትህ

አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በጥምቀትህ

### 51.ወተመሰሉ

ወተመሰሉ ሰብአ ዓይነ አባግዐ ላባ ወማይ/2/

ለኀበ አባግዕ ዘዮም/2/ወጥምቀት ዐባይ/2/

ትርጉም፡-የላባ በጎች ሰላዮችና ውሃ ለዛሬ በጎች (ከርስቲያኖች) ምሳሌ ሆነ

### 52. **ነድ ለማየ ባህር**

ነድ ለማየ ባሕር ከበቦ

ማየ ባሕር ኀበ የሐውር ጸበቦ

ትርጉም፡-እሳት የባህር ውሃን ከበበው የባህር ውሃም የሚሄድበት ጠፋው/ጠበበው/

### 53.ዮሐንስኒ ሀሎ ያጠምቅ

ዮሐንስኒ ሀሎ ያጠምቅ /2/

በሄኖን በቅሩበ ሳሌም/2/

ትርጉም፡-ዩሐንስ በሄኖን በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ያጠምቅ ነበር

### 54.ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ኄር/2/

እስመ ለዓለም ምህረቱ  እስመ ለዓለም/4/

እናመስግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ/2/

የዓለም ቤዛ ነውና የማሕፀንሽ ፍሬ/4/

ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ካንቺ ተወልዶ/2/

መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ/4/

በድንግልናሽ የወለድሽው ክርስቶስ/2/

የድኩማኖች ብርታት ነው የሕሙማን ፈውስ/4/

በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ዕዳችንን ፋቀ/2/

በቸርነቱ ጠብቆ ከበደል አራቀን/4/

ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም የዘከረ/2/

በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ/4/

ብርሃነ መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ/2/

ቅድስት ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ/4/

እመቤታችን እናታችን ማርያም/2/

የተማፀነሽ ይድናል ለዘለዓለም/4/

ድንግልናሽም ሳይለወጥ ወልድን የወለድሽ/2/

የጌታችን እናት ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ/2/

## 55.በኀል በኀል

በኀል በኀል ሰበአ ሰገል/4/

በኀል ሰብአ ሰገል ሰገዱለት/4/

ፀሐይ/2/ ፀሐይ ሠረቀ/2/

ፀሐይ ሠረቀ ክርስቶስ ተጠምቀ/4/

አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ /4/

የእግዚአብሔር መንፈስ ከላይ ወርዶልሽ

የዓለም መድኃኒት ተጠመቀብሽ

ድንግል ማርያም ንጽህት ቅድስት/4/

የጌታዬ እናት ምስጋና ይገባሻል

ከሴቶች ሁሉ አንቺን መርጦሻል

እልል እልል ደስ ይበለን/2/

ወልድ ተወልዶ ነፃወጣን

ዮሐንስ አጥምቆ ድል አገኘን

## 56.በዕደ ዮሐንስ

በዕደ ዮሐንስ ኢየሱስ ናዝራዊ /2/

ሰማያዊ /5/በዕደ ምድራዊ/2/

ትርጉም፡ሰማያዊው የናዝሬቱ ኢየሱስ በምድራዊው በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

### 57.ውስተ ማሕፀነ

ውስተ ማሕፀነ ድንግል ኀደረ ማሕፀነ ድንግል/2/

ሰማይ ወምድር ዘኢያገምሮ/2/ በማይ ተጠምቀ/2/

ትርጉም፡-ሰማይና ምድር የማይችሉት አምላክ በእመቤታችን ማኅጸን አደረ በውሃ ተጠመቀ

### 58.ክርስቶስ ተወልደ

ክርስቶስ ተወልደ ክርስቶስ ተወልደ/2/

ወለደነ ዳግመ እም መንፈስ ቅዱስ ወማይ/2/

ትርጉም፡-ክርስቶስ ተወልደ ተጠምቀ ክርስቶስ/2/

ዳግመኛ ወለደን ከውሃ ከመንፈስ ቅዱስ/4/

### 59.የዓለም በደል

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ

ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ

ጽድቅን ለመሥራት በደልን አጥፍቶ

የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ

አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ

የሰማያት ሰማይ የማይችለው ንጉሥ

ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ

ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ በመንፈስ

አዝ-----

ባሕር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ

ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ

እንደተናገረው ዳዊት በትንቢቱ

አዝ----

ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሠርት

መጣ በደመና ሰማያዊው አባት

እየመሰከረ የልጁን ጌትነት

አዝ---

እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ

መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ

በርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰይፎ

አዝ----

ባሕር ስትጨነቅ ተራራው ሲዘምር

ሰማዩ ሲከፈት ደመናው ሲናገር

ዓለም በዘሬው ቀን አየች ታላቅ ምሥጢር

## 60.ጥምቀተ ባሕር

ጥምቀት ባሕር ዮርዳኖስ ነያ/2/

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ/2/

ጌታችን ሲጠመቅ ባሕር ምን አለች

አልችለውም ብላ ወደ ኋላ ሸሸች

ብርሃነ መለኮት በወንዙ ሲሞላ

ዮርዳኖስም ሸሸ ሄደ ወደ ኋላ

አዝ---

አብ በመጣ ጊዜ ደመናውን ጭኖ

መንፈስ ቅዱስ ታየ በርግብ አምሳል ሆኖ

ለልጁ ምስክር ሊሰጥ ፈለገና

ቃሉን ተናገረ ሆኖ በደመና

አዝ---

ጌታችን ሲጠመቅ በሠላሳ ዓመት

ባሕር ኮበለለች ግዑዟ ፍጥረት

ሰማይ ተከፈተ ሆነልን ፀዓዳ

ምሥጢረ ሥላሴ ታወቀ ተረዳ

አዝ---

እልል በይ ዮርዳኖስ የጥምቀት መገኛ

የጽድቅ መሠረተ ድኅነታችን ለእኛ

ቀላያት አብሕርት ብዙዎች እያሉ

እንደምን ተመረጥሽ ዮርዳኖስ ከሁሉ

**61.ነፃነት አገኘን**

በዛሬው ጥምቀቱ እሰይ እሰይ ተነግሮን አዋጅ እሰይ እሰይ

ነፃነት አገኝ እሰይ እሰይ በእግዚአብሔር አብ ልጅ

እሰይ እሰይ ተወለደ/2/

ከሰማየ ሰማያት ወረደ

በቅዱስ ዮሐንስ ተጠመቀ

አብ መሰከረለት እሰይ እሰይ በደመና ሳለ እሰይ እሰይ

የምወደው ልጄ እሰይ እሰይ ይኸነው እያለ እሰይ እሰይ እሰይ

አዝ----

ጌታ በዮሐንስ እሰይ እሰይ ሊጠመቅ ሲል ገና እሰይ እሰይ

ወደ ኋላ ሸሸች እሰይ እሰይ ዮርዳኖስ ፈራና እሰይ እሰይ

አዝ----

እንደ አንበሳ ደቦል እሰይ እሰይ ተራሮች ዘለሉ እሰይ እሰይ

ዕጹብ ድንቅ ነው እሰይ እሰይ ግሩም ነው እያሉ እሰይ እሰይ

አዝ----

ውሃን ወይን አደረገ እሰይ እሰይ ከተጠራበት ቤት እሰይ እሰይ

የብርሃናት ጌታ እሰይ እሰይ የዓለም መድኃኒት እሰይ እሰይ

**62.ኅዲጎ ተስዓ**

ኅዲጎ ተስዓ ወተሰዓተ ነገደ

ማዕከለ ባሕር/2/ቆመ ማዕከለ ባሕር

ትርጉም፡-ዘጠና ዘጠኙን የመላእክት ነገድ ትቶ በባሕር መካከል ቆመ

**63.ሰላማዊ ብእሲሁ**

ሰላማዊ ብእሲሁ ቅዱሳን እደዊሁ/2/

እለ አጥመቃሁ/4/ለመድኅኔዓለም/2/

ትርጉም፡- ሰላማዊው ሰው እጆቹ የተቀደሱ ናቸው

መድኀኔዓለምን አጥምቀውታልና

### 64.ሰላም ለከ

ሰላም ለከ ኦ ፈለገ ዮርዳኖስ ዘተቀደስከ

በርደተ መንፈስ ቅዱስ/2/

ህየ ንሰግድ ኲልነ ኀበ ተጠምቀ እግዚእነ/2/

ትርጉም፡-በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የተቀደስክ የዮርዳኖስ ወንዝ

ሰላም ላንተ ይሁን

በዚህ ጌታ በተጠመቀበት ሁላችን እንሰግዳለን

### 65.ሶበ መጽአ ቃል

ሶበ መጽአ ቃል እም ሰማይ ለተናብቦ

ከበቦ/3/ለማየ ባሕረ መጽአ ነድ ለማይ ከበቦ

ትርጉም፡-ቃል ከሰማይ ለመናገር መጣ እሳት የባህርን ውሃ ከበበው

### 66.ቅዱስ እግዚአብሔር

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው

ዘኢይመውት/2/

ዘተወልደ እም ማርያም ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ተሣህለነ እግዚኦ/2/

ትርጉም፡-ከማርያም የተወለደው በዮርዳኖስ የተጠመቀው ቅዱስ

እግዚአብሄር ኃያልና የማትሞት ይቅር በለን

### 67.ቆመ ማዕከለ ባሕር

ቆመ ማዕከለ ባሕር ገብአ/2/

ወወጽአ በሰላም ወወጽአ በሰላም/2/

ትርጉም፡-በባህር መካከል ገባ/ቆመ/በሰላምም ወጣ

### 68.በዮርዳኖስ ተጠምቀ

በዮርዳኖስ ተጠምቀ/2/በሠላሳ ክረምት/2/

ከመ ይስዐር መርገማ ለሔዋን ዲበ ዕፀ መስቀል ተሰቅለ/2/

ትርጉም፡-በሠላሳ ዓመቱ በዮርዳኖስ ተጠመቀ የሔዋንን መርገም

ይሽር ዘንድ በእንጨት መስቀል ተሰቀለ

## 69.ተነሡ እነዘምር

ተነሡ እንዘምር ደስ ይበለን/2/

አምላካችን ተጠመቀልን/2/

## 70.አጥመቆ በማየ

አጥመቆ በማይ/2/

ዮሐንስ አጥመቆ በማይ/2/

ትርጉም፡-ዩሐንስ በውሃ አጠመቀው

## 71.ክርስቶስ

ክርስቶስ ተወልደ አማን ክርስቶስ ተጠምቀ አማን

ወለደነ ዳግመ እም ማይ/2/ዳግመ ዳግመ ወለደነ እም ማይ

ትርጉም፡-ከርስቶስ በእውነት ተወለደ ተጠመቀ ዳግመኛ ከውሃ ወለደን

## 72.ክርስቶስ ተወልደ

ክርስቶስ ተወልደ ወተጠምቀ

አስተርዕዮቱ አማን/4/

ትርጉም፡-ክርስቶስ ተወለደ ተጠመቀ መገለጡ እውነት ነው

## 73.ይቤሎ ኢየሱስ

ይቤሎ ኢየሱስ ለዮሐንስ አጥምቀኒ በማይ ከመ ይትቀደስ ማይ በር ኀወት ሰማይ

አጥመቆ ዮሐንስ ለኢየሱስ በፈለገ ዮርዳኖስ

ትርጉም፡-ኢየሱስ ዮሐንስን በሰማይ መከፈት ውሃ ይቀደስ ዘንድ በውኃ አጥምቀኝ አለው ዮሐንስም በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቀው

## 74.ነአምን

ነአምን/2/ክርስቶስሃ መድኀነ/2/

ዘዮሐንስ አጥመቆ በዮርዳኖስ/2/

ትርጉም፡-ዮሐንስ ያጠመቀው ክርስቶስ መድኀኒት መሆኑን እናምናለን

## 75.አስተርአየ

አስተርአየ ገሀደ አስተርአየ/2/

እንዘ ሕፃን ልሕቀ/2/

ትርጉም፡-እንደ ሕፃን አደገ በግልጥ ታየ

## 76.ይቤሎሙ ዮሐንስ

ይቤሎሙ ዮሐንስ ለሕዝብ ዘቦ ክልኤ ክዳናት የሀብ

አሐደ ለዘአልቦቱ/2/

ወካዕበ ይቤ ግበሩ ፍሬ ዘይደልወክሙ ለንስሓ

ትርጉም፡-ዮሐንስ ለሕዝቡ ሁለት ልብሶች ያሉት አንዱን ለሌለው ይስጥ አለ ዳግመኛም ለንስሓ የሚያበቃ ፍሬ አፍሩ አለ

## 77.ይትፌሣሕ ሰማይ

ይትፌሣሕ ሰማይ በልደቱ ወትትሐሠይ ምድር

በጥምቀቱ ለመድኀኔዓለም

ኸኸ ሶበ ይወርድ ወልድ ውስተ ምጥማቃት

ትርጉም፡-በመድኀኔዓለም ጥምቀት ወልድ ወደ መጠመቂያ ሥፍራ በወረደ ጊዜ ሰማይ በልደቱ ምድርም በጥምቀቱ ይደሰት

## 78.ዮሐንስ አጥመቆ

ዮሐንስ አጥመቆ ለኢየሱስ

ወገሠሦ ዘበዮርዳኖስ/2/

ትርጉም፡- ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው በዮርዳኖስም ዳሰሰው

## 79.ዮሐንስኒ

ዮሐንስኒ ያጠምቅ/2/

በሄኖን /4/በማዕዶተ ዮርዳኖስ/2/

ዮሐንስ ሲያስተምር ያጠመቀ

በጫካ በሜዳ ‹‹ ››

ገመል ጠጉር ለብሶ ‹‹ ››

ሆኖ ምድረ በዳ ‹‹ ›››

አምላኩን የሚወድ ያጠምቅ

ብዙ ሰው እያለ ‹›‹‹‹‹

ጌታውን ለማጥመቅ ‹‹‹‹ ›››

ዮሐንስ ታደሰ ‹‹‹‹ ›››

ተራራው ዝቅ ይበል ያጠምቅ

ጠማማውም ይቅና ‹‹ ››

እያለ አስተማረ ‹‹ ››

ሥርዓቱ ነውና ‹‹ ››

ከኀጢአት ተለዩ ያጠምቅ

በውሃ ተጠመቁ ‹‹ ››

መንግሥተ ሰማያት ‹‹ ››

እንዳለች እወቁ ‹‹ ››

**80.የሠላሙ መሪ**

የሠላሙ መሪ ሠላሙ ዳኛ/2/

አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ/2/

አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ/2/

የእግዚአብሔር መንፈስ ከላይ ወርዶብሽ የዓለም

መድኀኒት ተተመቀብሽ/2/

ድንግል ማርያም ያስገኘሽው ፍሬ/2/

ሕዝቦቹን ለማዳን ተጠመቀ ዛሬ/2/

እናንተ ተራሮች እግር ሳይኖራችሁ/2/

እንዴት እንደ ጊደር ሽቅብ ዘለላችሁ/2/

አዲስ ሙሽራ ሲመጣ እያያችሁ/2/

የዮርዳኖስ ምንጮች ስለምን ሸ ሻችሁ/2/

የገመል ደበሎ ለብሶ ቢታያቸው/2/

መጥምቁ መጥምቁ ዮሐንስ አውሬ መሰላቸው/2/

ወለደን በጥምቀት በመንፈስ ዳግመኛ/2/

የንጉሦች ንጉሥ የጻድቃን እረኛ /2/

አዳምን ሊጠራ የመጣው ሙሽራ/2/

በገሊላ መንደር ለሠርግ ተጠራ/2/

ሠርግ ቤት እንዳለ በክብር ተቀምጦ/2/

የወይን ጠጅ ውሃው ተለውጦ/2/

ለመልካሙ ሥራ እንግዲህ እንበርታ/2/

ከሰይጣን መገዛት ነጻ አወጣን ጌታ/2/

### 81.እንዘ ሕጻን

እንዘ ሕፃን ልህቀ በዮርዳኖስ ተጠምቀ/2/

በዮርዳኖስ /4/ ተጠምቀ በዮሐንስ /2/

ትርጉም፡- እንደ ሕፃን ሆኖ በትንሽ

በትንሹ አደገ በዮርዳኖስ

ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

### 82.እም ገሊላ

እምገሊላ/2/በዮሐንስ/2/

ኀበ ዮሐንስ/2/

ትርጉም፡-ከገሊላ ወደ ዮሐንስ ሄደ

### 83.ማየ ዮርዳኖስ

ማየ ዮርዳኖስ ሥሙር ወጤግሮስ/2/

ኀበ ወረደ መንፈስ ቅዱስ/2/

ትርጉም፡-መንፈስ ቅዱስ የወረደበት የዮርዳኖስ እና የጤግሮስ ውሃ የተወደደ ነው

### 84.በመንፈስ የሐውር

በመንፈስ የሐውር ወበኀይለ ኤልያስ/2/

አልቦ ዘየዐብዮ ለዮሐንስ/2/

ትርጉም፡-በኤልያስ ኀይል በመንፈስ ይሔዳል ዮሐንስን የሚበልጠው የለም

### 85.በመንፈስ የሐውር

በመንፈስ የሐውር እምኀይል ውስተ ኀይል/2/

ካህን/2/ወነቢይ/2/ ዮሐንስ መጥምቅ/2/

ትርጉም፡-በኤልያስ መንፈስ ከኀይል ወደ ኀይል ይሔዳል መጥምቅ ነቢይና ካህን ዮሐንስ

### 86.እንኳን አደረሰን

እንኳን አደረሰን ለዛሬዋ ቀን/2/

ሲወለድ ሲጠመቅ አየነው/2/ የዓለሙን መድኅን

### 87. ከላይኛው ሀገር

ከላይኛው ሀገር ከሰማየት ወርዶ

ከድንግል ማርያም በስጋ ተወልዶ

ድንግል ማርያም ሆይ ያስገኘሽው ፍሬ

ለህዝቦች አርአያ ተጠመቀ ዛሬ

መለኮት ኀያሉ ተኝቶ በበረት

እጅ መንሻ አመጡለት ሦሥት ነገስታት

ድንግል ማረያም ሆይ ያስገኘሽው ፍሬ

ለህዝቦች አርአያ ተጠመቀ ዛሬ

ሎሌ ወደ ጌታውነው እንጂ የሚሄድ

ጌታ እንዴት ይመጣል አገልጋዩ ዘንድ

አዝ

አጠምቅ ነበረ ባንተ ስም ህዝቡን

እንዴት ብዬ ላጥምቅ አንተን ጌታዬን

አጥምቀኝ እኔን እንዲህም እያልክ

ከሳቴ ብርሃን ወልዱ ለብሩክ

አዝ

እንደዚህ እያለ ሲያጠምቅ በልብ

መንፈስ ቅዱስ መጣ በአምሳለ ርግብ

አብም መሰከረ በደመና ሳለ

የምወደው ልጄ ይኸ ነው እያለ

አዝ

ወደሀገራቸው ለመሄድ ሲነሱ

በሄሮድስ በኩል እንዳይመለሱ

መልአኩ ነግሯቸው እነሱም አምነው

በሌላ ጎዳና ገቡ አገራቸው

አዝ

ሰማይና ምድርን እንዳልደነገገ

ከህጻናት ጋራ በገሊላ አደገ

ከግብጽ ሲመለስ ኖሮ በስደት

ናዝራዊ ለመባል ኖረ በናዝሬት

**88. አምላክ ከዮርዳኖስ**

አምላክ ከዮርዳኖስ (2)ተጠምቆ ሲወጣ

ሰማያት ተከፍተው(2) ከሰማይ ቃል ወጣ

ቃሉም እንዲ ነበር (2) እንደሚከተለው

የምወደው ልጄ(2) ይህ ነው የሚል ነው

ዘጠና ዘጠኙን (2)መለአክቱን ትቶ

አምላክ ተጠመቀ(2)በዮርዳኖስ ገብቶ

ዕጹብ ድንቅ ነው (2) ይገርማል በውኑ

ሰማያዊ አምላክ (2) ምድራዊ መሆኑ

አብ የነገረለት (2) በደመና ወርዶ

ተጠምቆ አዳነን (2) ከድንግል ተወልዶ

## የቃና ዘገሊላ መዝሙር

## ጥር 12 ቀን

**89.ይትባረክ እግዚአብሔር**

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል

ዘገብረ ዐቢየ ወመንክረ ባሕቲቱ

ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ ቅዱስ

ወይምላዕ ስብሐቲሁ ኩሎ ምድር ለይኩን ለይኩን

ትርጉም፡- ብቻውን ታላላቅ ተአምራትን ያደረገ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ ቅዱስ የሆነ የምስጋናው ስምም ይባረክ ምስጋናውም ምድርን ሁሉ ይሙላ ይሁን ይሁን

**90.እንዘ ስውር**

እንዘ ስውር እምኔነ ይዕዜሰ ክሡተ ኮነ/2/

ተአምረ ወመንክረ ገብረ መድኀኒነ በቃና ዘገሊላ ከብካበ ኮነ

ማየ ረሰየ ወይነ/2/

ትርጉም፡-ከእኛ የተሰወረ ሲሆን አሁን ግን የተገለጠ ሆነ በገሊላ አውራጃ መድኀኒታችን ውሃውን ጠጅ አደረገ ድንቅ ተአምሩን ገለጠ ሠርግም ተደረገ

**91.በቃና ዘገሊላ**

በቃና ዘገሊላ /2/

ዘገሊላ ከብካብ ኮነ/4/

ትርጉም፡-በቃና ገሊላ ሠርግ ተደረገ

**92.ወይነ ቃና**

በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ /2/

ወይነ ቃና (2)በቤትከ ኮነ/4/

ትርጉም፡-እንደሰማን እንዲሁ አየን የቃና ወይን በቤትህ ተደረገ

**93.እንዘ ስውር**

እንዘ ስውር እምኔ ይዕዜሰ ክሡተ ኮነ/2/

ወለማይኒ ረሠዮ ወይነ/4/

ትርጉም፡-ዝኒ ከማሁ

**94.ተአምረ ወመንክረ**

ተአምረ ወመንክረ ገብረ መድኃኒነ/2/

በቃና ዘገሊላ/2/ ከብካበ ኮነ/2/

ትርጉም፡-ዝኒ ከማሁ

**95.አዳም ያልተወው**

አዳም ያልተወው እንደተሰደደ

እሰይ የምስራች ዛሬ ተወለደ/2/

አምላካችን መድኒታችን

ተወለደ ለነፃነታችን/2/

አዳም ያልተወው እንደተጨነቀ

እሰይ የምስራች ዛሬ ተጠመቀ/2/

አዝ---

ሠርግ ቤት እንዳለ በክብር ተቀምጦ

የወይን ጠጅ ሆነ ውሃው ተለውጦ/2/

አዝ---

በገሊላ መንደር ይህንን ተአምር ሠራ

እጅግ ያስደንቃል የጌታችን ሥራ/2/

አዝ---

ጌታችን አንዲት ቀን ያደረገው ተአምር

ሲያስደንቅ ይኖራል ይህን ሁሉ ፍጡር/2/

**96.ዘበዳዊት**

ዘበዳዊት ተነበየ ወበዮሐንስ ጥምቀተ ኅርየ

በቃና ዘገሊላ/2/ማየ ወይነ ረሰየ

ትርጉም፡-በዳዊት እንደተናገረ በዮሐንስ ጥምቀትን መረጠ በገሊላ ቃና ውሃን ወይን አደረገ

**97.መዓዛ ቃልከ**

በቃና ዘገሊላ ማየ ወይነ ረሰየ/2/

መዓዛ ቃልከ ይትወከፍ ጸሎትየ/4/

ትርጉም፡-በገሊላ ቃና ወሃን ወይና አደረገ የቃልህ መዓዛ ጸሎቴን ይቀበል

98. **አማኅኩኪ**

አማኅኩኪ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከብካብ ኮነ በቃና ዘገሊላ/2/

ደምፀ እንዚራ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር/2/

ትርጉም፡-ቅድስት ቤተክርስቲያን እጅ ነሳሁሽ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ተደረገ በእግዚአብሔር ቤትም የበገና የመሰንቆ ድምፅ ተሰማ

**99.አንክርዎ**

አንከርዎ ለማይ አንከርዎ/2/

አእኰትዎ ለኢየሱስ/2/

ትርጉም፡-ወደ ወይን ጠጅ የተለወጠውን ውሃ አደነቁት ኢየሱስንም አመሰገኑት

የቅዱስ ጊዮርጊስ መዝሙር

ጥር 18

**100. ከመጸበል**

ከመጸበል ዘነፋስ ዘረውዎ ደብረ ይድራስ(2)

ለብፁዕ ወለቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰማዕት(2)

ትርጉም፡-ነፋስ ትቢያውን እንዲበትነው ብጹዕ የሚሆን ቅዱስ ጊዮርጊስ ዐጽሙን ይድራስ በተባለ ተራራ ላይ በተኑት

**101. በበግማድ**

በበግማድ ሥጋሁ መተሩ(3) (2)

ቅዱስ(3) ጊዮርጊስ ሞዖሙ ለጸሩ(2)

ትርጉም፡-በየክፍሉ ሥጋውን ቆራረጡት ቅዱስ ጊዮርጊስ ጠላቶቹን አሸነፏቸው

**102. አማን በአማን**

አማን በአማን(2) ፀሐየ ልዳ(2)

ፀሐየ ልዳ ኮከበ ፋርስ(4)

ትርጉም፡-በእውነት የልዳ ፀሐይ የፋርስ ኮከብ ነህ

**103. ኀበ ተገብረ**

ኀበ ተገብረ ተዝካርከ ወኀበተነበ መጽሐፈ ገድልከ(2)

ህየይኩን ሣህል ወምሕረትህየ ይኩን ሊቀ ሰማዕታት(2)

ትርጉም፡- መታሰቢያህ በተደረገበት የገድልህ መጽሐፍ በተነበበበት የሰማዕታት አለቃ በዚያ ምሕረት ቸርነት ይሁን

**104. አክሊሎሙ**

አክሊሎሙ አንተ ለሰማዕት(2)

ወአስተርአየ ገሀደ ከመሰብእ(2)

ትርጉም፡ሰማዕታት አክሊላቸው አንተ ነህ እንደሰው በግልጽ ታየ

**105. ገባሬመንክራት**

ገባሬ መንክራት ጊዮርጊስ በአቁጽሎ ይቡስ ዓምድ(2)

ተራድአነ በገሃድ ተራድአነ(2)

ትርጉም፡-ደረቅን በማለምለም ድንቅን የምታደርግ ጊዮርጊስ ሆይ በግልጽ ተራዳን

**106. ሰአልለነ**

ሰአልለነ ጊዮርጊስ(2) ኀበእግዚእ(2)

ወጸሊ በእንቲአነ አረድዎ ወገመድዎ ወዘርዉ ሥጋሁ ከመአመድ(2)

ትርጉም፡-ጊዮርጊስ ሆይደ ወደ ጌታ ስለእኛ ለምን

ሥጋውን ቆራርጠው እንደ አመድ በተኑት

**107. ከመጸበል**

ከመጸበል ዘነፋስ ዘረውዎ ይድራስ(2)

ለብጹዕለቅዱስ(3) ጊዮርጊስሰማዕት(2)

ትርጉም፡ብጹዕና ቅዱስ የሚሆን ሰማዕቱ ጊዮርጊስ ነፋስ ትቢያን እንዲበትነው በይድራስ ተራራ በተኑት

**108. ከመጸበል**

ከመጸበል ዘነፋስ ዘረውዎ ደብረ ይድራስ(2)

ወወገርዎ(6) ለጊዮርጊስ(2)

ትርጉም፡- ዝኒ ከማሁ

**109. ዘረው ሥጋሁ**

ዘረው ሥጋሁ(2)

ኀኸ(5) አባ ጊዮርጊስ  መንግሥተ ክብር ወረ በሰላም

ትርጉም፡-ሥጋውን በተኑት አባታችን ጊዮርጊስ በሰላም የክብርን መንግሥት ወረሰ

**110. ነአምን**

ነአምን ዜናሁ ዜናሁ ለጊዮርጊስ (2)

እምኀበ አቡሁ (2) ነአምን ዜናሁ ነአምን(2)

ትርጉም፡-ከአባቱ ዘንድ የሆነውን የጊዮርጊስን ዜና እናምናለን